# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ::" (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 – 9395

**ሐምሌ 1995 July 2003** "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ፤ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል::" (ኢሳ 54÷13)

# ቆንጂትና የአንገት ሐብል

አንዷት የአምስት ዓመት ቆንጅዬና ደስተኛ ልጅ ነበረች:: እርሷም ከዕለታት አንድ ቀን ከእናቷ ጋር ገበያ ሄደች:: በገበያውም መሐል እናቷን ተጠግታ ቆማ ሳለች በድንገት ዓይኗ በአንድ ውብና አንጸባራቂ ጥቅል ጌጥ ላይ አረፈ:: እርሱም በሐምራዊ መጠቅለያ የተጠቀለለ ከዕንቁ አምሳል የተሠራ የአንገት ሐብል ነበረ::

ወዲያውም ልጅቱ እናቴ÷እናቴ÷ ይህን ግዢልኝ:: እባክሽን÷እማምዬ÷ ይህን ሐብል ግዢልኝ፤ እያለች እናቷን መወትወት ጀመረች:: ወዲያውም እናትየዋ ሐብሉን አንሥታ ዋጋውን ተመለከተች:: <u>ዋጋው አንድ ብር ከዘጠና አምስት ሣንቲም ነበር::</u> ከዚያም ዘወር ብላ ወደ ልጂቱ ተመለከተችና:- ይህን መግዛት አልችልም:: ሁለት ብር ሊሆን ምን ቀረው? አለቻት::

ልጅቱም መወትወቷን በቀጠለች ጊዜ እናቷ አዘነችላትና:- እቤት ውስጥ ተጨማሪ ሥራ ሠርተሽ በአጭር ጊዜ ውስጥ በራስሽ ገንዘብ ይገዛልሻል:: ደግሞም ልደትሽ በሚቀጥለው ሳምንት ስለ ሆነና÷ከአያትሽ ገንዘብ ስለምታገኚ የሚበቃሽን ያህል ይኖርሻል ብላ አጽናናቻት::

ልጅቱም ቤቷ እንደ ደረሰች ወዲያው ያጠራቀመቻቻቸውን ሣንቲሞች አውጥታ መቁጠር ጀመረች:: 17 ሣንቲም ነበራት:: ከእራት በኋላ ሳህኖችን በማጠብና በመላላክ እናቷን ለማስደሰት ተጋች:: ወደ ጎረቤትም ሄዳ በመርዳት ተጨማሪ ገንዘብ አገኘች:: በልደቷም ቀን አያቷ አንድ ብር ሰጧት:: በመጨረሻም ሐብሉን ለመግዛት የሚያስፈልገውን አንድ ብር ከዘጠና አምሥት ሣንቲም አጠራቀመች::

ቆንጂት ሐብልዋን እጅግ ወደደች:: ትልቅና ቆንጆ ሴት ስለሚያስመስላት በጣም ትኮራበት ነበር:: ሳታደርገው የትም አትሄድም ነበር:: መዋዕለ ሕፃናት ሆነ ቤተ ክርስቲያን÷እንዲሁም በመኝታዋ ላይ እንኳን ሳይቀር ሐብሏን ታደርግ ነበር:: ገላዋን ስትታጠብ ወይም ዋና ስትሄድ ብቻ ነበር የምታወልቀው:: ይህንንም የምታደገው÷ እናቷ ሐብሉ ከረጠበ አንገቷን እንደሚያጠቁር ስለ ነገረቻት ነበር::

ቆንጂት በጣም የሚወዳት ደግ አባት ነበራት:: በየምሽቱ ወደ መኝታዋ ስትሄድ የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር አቁሞ÷ ወደ አልጋዋ በመሄድ ተረት ይነግራት ነበር:: አንድ ምሽት ተረት ነግሯት ከጨረሰ በኋላ:- "ቆንጂትዬ÷እኔን አባትሽን ትወጂኛለሽን?" ሲል ጠየቃት:: እርሷም÷ አዎን አባቴ፤ እንደምወድህ አንተም ታውቃለህ አለችው:: እርሱም መልሶ:-"እንግዲያውስ ሐብልሽን ስጪኝ" አላት::

እርሷም መልሳ:- "አይሆንም አባቴ:: እንዴት ሐብሌን ትጠይቀኛለህ ? ከሌሎቹ መጫወቻዎቼ የመረጥኸውን መውሰድ ትችላለህ:: ሐብሌን ግን አትንካብኝ" ስትል መለሰችለት:: አባትየውም "መልካም ነው ልጄ÷ እኔ አባትሽ ምን ጊዜም እወድሻለሁ:: በሰላም እደሪ" ብሎአት÷ ግምባሯን ስሞአት ወደ ክፍሉ ሄደ::

ከሳምንት በኋላ በመኝታ ሰዓት÷የቆንጂት አባት፡ እንደ ልማዱ ተረት ከነገራት በኋላ "ቆንጂትዬ:- እኔን አባትሽን ትወጂኛለሽን?" ሲል ጠየቃት::እርሷም "አዎን እንጂ አባባ÷ እንደምወድህ አንተም ታውቃለህ" ስትል መለሰችለት:: አባቷም "እንግዲያውስ ሐብልሽን ስጪኝ" አላት::

ቆንጂትም "አይሆንም አባባ÷ ሐብሌንስ አልሰጥህም:: ለልደቴ የተሰጠኝን አዲሱን አሻንጉሊቴን መውሰድ ትችላለህ:: የመረጥኸውን መጫወቻዬን መውሰድ ትችላለህ:: ነገር ግን ሐብሌን አትንካብኝ" ስትል መለሰችለት::

አባትየውም "መልካም የእኔ ቆንጆ÷ መልካም እንቅልፍ÷ እኔ አባትሽ ሁልጊዜ እወድሻለሁ::በሰላም እደሪ" ብሎአት ከሳማት በኋላ÷ ወደ ሥፍራው ሄደ::

ከጥቂት ቀናት በኋላ÷ አባትየው እንደ ልማዱ ወደ መኝታ ክፍልዋ ሲገባ ቆንጂት እግሮቿን አጣምራ በአልጋዋ ላይ ተቀምጣ ስትተክዝ አገኛት:: ሲጠጋትም ትላልቅ የዕምባ እንክብል በእነዚያ የተከዙ ጉንጮቿ ላይ ተንከባልለው ሲወርዱ ተመለከተ:: እርሱም ደነገጠና÷ "ምን ነው ቆንጂትዬ? ምን ሆነሻል?" ሲል ጠየቃት::

እርሷም ምንም ሳትመልስ እየተንሰቀሰቀች እጅዋን ወደ አባትዋ ዘረጋች:: እጅዋንም ስትከፍት ሐብሉ ነበረበት:: አከላቱን ቆርጦ ለሰው እንደሚሰጥ ሰው እያመማት "እንካ አባቴ :: ሐብሌን ተቀበል" ብላ ሰጠችው::

አባቷም እንባ እየተናነቀው:- በአንድ እጁ ዝገት የጀማመረውን አርትፊሻል ዕንቁዋን ተቀበለና በሌላኛው እጁ ደግሞ ከኪሱ እውነተኛ የዕንቁ ሐብል አውጥቶ ሰጣት::

<u>*ይህንን ዕውነተኛ ዕንቁ ከመጀመሪያውም ጀምሮ አባቷ አዘጋጅቶላት ነበረ::*</u> ሆኖም ቆንጂት የማይረባውን አርቲፊሻል ሐብልዋን ለመስጠት ፈቃደኛ እስክትሆን ድረስ ነበረ የጠበቀው:: ቆንጂት አባቷ ሐብልዋን እንዲትሰጠው ሲጠይቃት እውነተኛ ስጦታ ሊሰጣት አስቦ እንጂ ለራሱ አርቲፊሻል ሐብል አስፈልጎት እንዳልነበረ ልትረዳ አልቻለችም::

የሰማዩ አባታችንም እንደዚሁ ነው:: ዘለቄታ ያለው ክቡር ስጦታ ካዘጋጀልን በኋላ:- ርካሽና ዘላቂነት የሌለውን ነገራችንን እንድንሰጠው ይጠይቀናል:: ይህም ጊዜአችን ሊሆን ይችላል:: ወይም በቋሚ ፆም ፀሎት በእርሱ ፊት ጊዜ እንድናሳልፍ ይሆናል:: ወይም ማንኛውንም እኛ የምንወደውን ነገራችንን ሊጠይቀን ይችላል:: ከዚያም ከእኛ የእሽታ መልስ እስኪያገኝ ድረስ በረከታችን ታስሮ ይቀመጣል::

ወገኔ:- እግዚአብሔር በጐና ያማረ የተሻለም ስጦታ አዘጋጅቶልሃል:: ነገር ግን መታዘዝህን ያይ ዘንድ÷እንድትሰጠው የጠየቀህ ነገር አለ? የሙጥኝ ብለህ የያዝኸው÷ዘለቄታ የሌለው÷ የማይጠቅም ነገር ምንድን ነው? ባሕሪይ ነው? ዓመል ነው? ሥራ ነው? ወዳጅነት ነው? ሐብት ነው?

አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን ነገር በግልጽ መረዳት ያስቸግራል:: ሆኖም ግን በአንድ ነገር እርግጠኞች መሆን እንችላለን:: <u>*ጌታ አምላካችን የተሻለ ስጦታ ሳያዘጋጅልን ምንም ነገር ከእኛ አይጠይቅም*</u> *እግዚአብሔር ይመስገን::*

---

# የዌብ ገጽ

ከእግዚአብሔር ፍቅር ወንጌላዊ የደብዳቤ አገልግሎት በዌብ ገጽ ላይ ተዘጋጀ:: የአማርኛ ፊደል ሳይኖራችሁ ደብዳቤአችንን ማተም እንድትችሉ:- አዶቢ አክሮባትን በነፃ መቅዳት ይቻላል:: ደብዳቤዎቹን ስትከፍቱ ÷ አማርኛው ወዲያው ባይገለጥ ጥቂት ይታገሡ:: እንደ ኮምፒውተራችሁ ፍጥነት ጊዜ ይወስዳል:: አድራሻችን እነሆ:-

www.gods-love-ethiopia.com

---

# ምሥጋና

*ወንድማችን መጋቢ ታምራት በዳኔ ከኒውዮርክ፥ የምታደርግልንን ርዳታ በመቀጠል የላክህልን ስጦታ ደርሶናል። እህታችን ገነት ሸዋረገድ ከካንሳስ የፍቅር ስጦታሽን በምስጋና ተቀብልናል።*

*በአገልግሎታችን ስለምትተባበሩን ወገኖቻችን ሁሉ ጌታን እጅግ እናመሰግናለን። ጌታ ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ለመንግሥቱ ሥራ እጆቻችሁን በቸርነት ለምትዘረጉ ሁሉ የቸርነት እጆቹን ይዘርጋላችሁ:: አሜን::*

---

# አድራሻዎችን ላኩልን

የምታውቋቸውን ሰዎች አድራሻ በደብዳቤ ወይም በኢሜይል ላኩልን::

**www.gods-love-ethiopia.com**

# ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ሊመጣ ነው

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከኃጢአቱ ለማዳን ወደ ዓለም መጥቶ በ ሰው አምሳል ተወልደ:: ነፍሱንም ስለ በ ደላችን በመስቀል ላይ አሳልፎ ሰጠ:: ሁሉን የሚችለው ፈጣሪ በፍጥረቱ እጅ ተወግቶ ሞተ:: "እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም÷ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደ ረገ÷በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ÷ ለሞትም ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ::" (ፊልጵስዩስ 2÷6-8)

"ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ÷ ተ ቀበረም÷ መጽሐፍ እንደሚል በሦስተኛ ው ቀን ተነሣ" (1ቆሮንቶስ 15÷4)

ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛ ሙርትና ለሌሎችም በርካታ ምዕመናን ታየ:: የታላቁንም ተልዕኮ መመሪያ ሰጣ ቸው:: "ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸ ው ሰውራ ተቀበለችው:: እርሱም ሲሄድ (ሐዋሪያቱ) ወደ ሰማይ ትኵር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ ÷ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች (መላዕክት) በአጠገባቸው ቆሙ፤ ደግሞም:- የገሊላ ሰዎች ሆይ÷ ወደ ሰማይ እየተለከታችሁ ስለ ምን ቆማ ችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣ ው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያች ሁት÷ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው:: "
(የሐዋሪያት ሥራ 1÷ 11)

ጌታችን በደመና ውስጥ ከፍ ከፍ ብ ሎ ወደ ሰማይ እንደ አረገ÷ በዚያው መ ልክ ተመልሶ የሚገለጥ መሆኑን ከቃሉ እንረዳለን:: በየትኛው ዓመት÷ ወርና ዕለ ት እንደሚመለስ ግን ከእግዚአብሔር በ ቀር ማንም ያውቅ ዘንድ አልተሰጠውም: በውድቅት ሌሊት በዕንቅልፍ ወቅት ሊሆ ን ይችላል:: ንቁዎች ብቻ በሚነቁበት ሰዓት÷ ጐሕ ሲቀድድ ማለዳ ወይም በጠ ራራው ፀሐይ በዕኩለ ቀንም ከተፍ ሊል ይችላል::እርሱ ራሱ እንዲህ ሲል አስጠን ቅቋል:: "እንግዲህ በማታ ቢሆን ወይም በዕኩለ ሌሊት ወይም ዶሮ ሲጮኽ ወይ ም በማለዳ ቢሆን ባለቤቱ መቼ እንዲመ ጣ አታውቁምና ድንገት መጥቶ ተኝታ ችሁ እንዳያገኛችሁ ስለዚህ ትጉ::" (የማር ቆስ ወንጌል 13÷35-36)
በተጨማሪም:- "ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ÷ የሰው ልጅ በማታስ ቡበት ሰዓት ይመጣልና::" ይላል::(ማቴዎስ 24÷44)

አንዳንዶች ጌታ በዚህ ዓመት ይመለሳ ል በማለት ለሰው ያልተፈቀደውን ነገር ሲተነብዩ ተሰምቶአል:: ሆኖም "ስለዚያ ች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብ ቻ በቀር የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ ል ጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም::" በማለት ጌታ አስቀድሞ አስጠንቅቆናል:: (የማቴዎስ ወንጌል 24÷36)

ጌታ አይዘገይም:: አመጣጡም እንደ መብረቅ ነው:: "... መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ የሰው ልጅ (የኢየሱስ) መምጣት እንዲሁ ይሆ ናልና ..." (የማቴዎስ ወንጌል 24÷27)

እንደ ሌባ በድንገት ይመጣል::"የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤" (2 ጴ ጥሮስ 3፤10) ስለዚህ "... ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር:ስለ ትዳርም በማሰብ:እን ዳይከብድ÷ያ ቀንም በድንገት እንዳይመ ጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤በምድር ሁ ሉ ላይ በሚቀመጡ ሁሉ እንደ ወጥመድ ይደርስባቸዋልና:: (የሉቃስ ወንጌል 21÷34-35)

ጌታ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ለሁሉ ም እንደ ሥራው መጠን ዋጋውን ይከፍ ለዋል:: "እነሆ÷በቶሎ እመጣለሁ÷ ለእያ ንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ::" (ራዕይ 22÷12)
"ለእናንተም የምነግራችሁን ለሁሉ እላለ ሁ፤ ትጉ::" (የማርቆስ ወንጌል 13÷37)

# የመመለሱ ምልክቶች

ምንም እንኳን የጌታን ምጽዓት ቀኑን ና ሰዓቱን ማወቅ ባንችልም የጊዜውን መ ቅረብ የምንረዳበት ምልክቶች ተሰጥተው ናል:: እንዲህ ይላል:: "ምሳሌውን ከበለስ ተማሩ ጫፍዋ ሲለሰልስ፡ ቅጠልዋም ሲያ ቈጠቍጥ ÷ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታ ውቃላችሁ፤ እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደ ቀረበ እወቁ::"
(የማቴዎስ ወንጌል 24÷32-33)

ጦርነትና የጦርነት ወሬ ማቴ 24÷6

ሕዝብ በሕዝብ÷መንግሥት በመንግሥት ላይ መነሣት ማቴ 24÷7

ራብ÷ቸነፈር÷የምድር መናወጥ ማቴ 24÷7
የዓመፃ ብዛትና የፍቅር መቀዝቀዝ (ማቴ 24÷12)

ሐሰተኛ ነቢያት÷ክርስቶስ ነን የሚሉት መነሣት (ማር 13÷ 22)

በኖሕ ዘመን እንደ ነበረው ብዙ ሰዎች አለማመናቸውን ይቀጥላሉ:: (ማቴ 24÷37)

በሰማይ ላይ ምልክት ይሆናል፡ አሕዛብ በፍርሃት ይጨነቃሉ:: (ሉቃስ 21÷25)

ሰዎችም በዓለም ከሚወርደው ፍርሃት የተነሣ ልባቸው ይከዳቸዋል:: (ሉቃስ 21÷26)

ሰዎች ሰላም ነው፤ምንም ችግር የለም ይ ላሉ:: (1 ተስሎንቄ 5÷3)

የሚያስጨንቅ ዘመን ይሆናል:: (2 ጢሞቴዎ ስ 3÷1-5)

ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላንና ሃይማኖተኛ መምሰልን ይወዳሉ:: (2 ጢሞ ቴዎስ 3÷1-7)

ክፉዎች እየከፉ ይሄዳሉ:: (2 ጢሞቴዎስ 3÷13)

ሰዎች አለአግባብ ሐብት ይሰበስባሉ:: (ያዕቆብ 5÷1-5)

ስለ ጌታ መምጣት የሚዘበቱ ይታያሉ:: (2 ጴጥሮስ 3÷3-7)

ሰዎች ዘባቾችና የሚያማርሩ÷ እንደ ገዛ ምኞታቸው መሆን የሚወዱ ይሆናሉ:: (ይሁዳ 16፤17፤18)

አሁንም ኃጢአተኛነት እየበዛ÷ፍቅር እየ ቀዘቀዘ÷ ክፋትና ሽብር እየገነነ ነው:: ዓ ለማዊ ምኞት÷አመንዝራነትና መፋታት ወንድ ከወንድ:- ሴት ከሴት የግብረ ሥ ጋ ብልሽት÷ የወጣቶች ለወላጆቻቸው አ ለመታዘዝ÷ ወዘተ ከምን ጊዜውም አይሎ አል:: በነገድ በጐሳ መለያየትና መጣላት እየተለመደ መጥቶአል:: እነዚህ ሁሉ የጌ ታችንን መምጫ መቃረብ ያመለክታሉ:: መገለጡን ኃጢአተኞች ይፈራሉ:: ቅዱሳ ን ግን "ጌታ ኢየሱስ ሆይ÷ና" ይላሉ:: አንተስ? አንቺስ?



*የማቴዎስ ወንጌል*
11÷28

# *ጽድቅ*

*"አሁን ግን እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያጸድቅበት መንገድ ከሕግ ነፃ ሆኖ ተገልጦአል፤ይህም በሙሴ ሕግ ና በነብያት ተመስክሮአል:: ስለዚህ እግዚአብሔርም ምንም ልዩነት ሳያ ደርግ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ት ሁሉ ጽድቅን ይሰጣል:: ምክንያቱ ም ሰዎች ሁሉ ኃጢአት ሠርተዋል፤ እግዚአብሔር የሰጣቸውንም ክብር አጥተዋል:: ስለዚህ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በፈጸመው በአዳኝነት ሥራ በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ይጸድቃሉ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን መ ሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው ፤ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ በደሙ የኃጢአታቸ ውን ይቅርታ እንዲያገኙ ነው ፤ እግዚአብሔር ይህን ማድረጉ የቀድ ሞውን ኃጢአት እንዳልነበረ በመቁ ጠር የራሱን የጽድቅ መንገድ ለመግ ለጥ ነው:: በአሁኑም ዘመን እግዚአ ብሔር ራሱ ጻድቅ መሆኑን የሚያሳ የው በኢየሱስ የሚያምኑትን ሁሉ በማጽደቅ ነው:: እንግዲህ የምንመካ በት ነገር ምን አለ? በምንም አንመ ካም፤ የማንመካበትስ ምክንያት ምን ድንነው?ሕግን ስለምንፈጽም ነውን? አይደለም፤ነገር ግን በእምነት ብቻ ነ ው:: ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን የ ሚያጸድቀው ሰው የሕግን ሥራ በ መፈጸሙ ሳይሆን÷በእምነት መሆኑ ን አንገነዘባለን::"* (ሮሜ 3÷ 21-28 አዲሱ ትርጉም)

❖❖❖❖❖❖

*"በአሁኑም ዘመን እግዚአብሔር ራ ሱ ጻድቅ መሆኑን የሚያሳየው በኢየ ሱስ የሚያምኑትን ሁሉ በማጽደቅ ነው:: (ሮሜ 3÷26 ኣዲሱ ትርጉም)*

*"አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመ ሰከረለት የእግዚአብሐር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል÷እርሱም÷ለሚያም ኑ ሁሉ የሆነ÷ በኢየሱስ ክርስቶስ በ ማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው::" (ሮሜ 3÷21-22)*
*የእግዚአብሔርን ጽድቅ ተቀብለሃ ል? ዛሬ ብትሞት የሚያድን ጽድቅ አለህ? የእግዚአብሔርን ጽድቅ በነፃ መቀበል ትሻለህ? የሚከተለውን ፀሎ ት ከልብህ በማመን በዕውነት ፀልይ፡ ጌታ እግዚአብሔር በሕይወትህ ውስ ጥ አስደናቂ ለውጥ ማድረግ ይጀም ራል::*

*ፀሎት:- ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ሰውን ለማጽደቅ የሰጠኸው ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው ስለ ኃ ጢአቴ መሆኑን አምናለሁ:: ከኃጢአ ት ተግባሬ እመለሳለሁ:: ከአሁን በኋ ላም በቃልህ መሠረት እኖራለሁ:: ወደ ጽድቅህ ተቀበለኝ:: ስለ ስምህ:: አሜን::*
*(አድራሻችን በመግቢያው ላይ ይገኛ ል:: ጻፉልን::)*

*ኢየሱስ ጌታ ነው:: ጌታ ይባርክህ::*